| ስለ ህጻናት መበደል እናቸልተኝነት መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ |
|---|
| ስለ በጎ ፈቃደኝነት በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች: 2026-2027 |

Montgomery County Public Schools

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎቻችንን ጥረቶች ለማገዝና ለማበልፀግ በት/ቤቶቻችን ለሚሰሩ በጎ-ፈቃደኞች ከፍ ያለ አክብሮት አለው። እንደ ማህበረሰብ፣ ለተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ እና አቅማቸውን የሚያጎለብት አካባቢ የመፍጠር የጋራ ኃላፊነታችንን እንገነዘባለን። እነዚህ አዘውትረው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs) የተዘጋጁት መልሶች ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና እና ዳራ የማጣራት ተግባር ያገለግላሉ።

ይህ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን የያዘ ሰነድ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደንቦች ጋር የሚጣጣም እና የተደገፈ ነው። ፖሊሲ JHC፣ የህጻናት በደል እና ቸልተኝነት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደንብ JHC-RA፣ በህጻናት ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደንብ IRB-RA፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ በጎ ፈቃደኞች። በጉስቁልና እና በቸልተኝነት የተተወ-የተተወች ልጅ ድረ-ገጽ "Child Abuse and Neglect website" ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ https://www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect/

## ጎብኚዎችን የመቀበል ስርዓት፡-

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ 1፡- ጎብኚዎች፣ በጎፈቃደኞች ጭምር ትምህርት ቤት በሚደርሱበት ወቅት ምን ማድረግ አለባቸው?** | **መ 1፡-** በተመደበው የትምህርት ሰዓት፣ ጎብኚዎችና በጎ ፈቃደኞች ጭምር ሁሉም (VMS) በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤቶች ግቢ ለመግባት መመዝገብ አለባቸው። |
| **ጥ 2፡- የጎብኚዎች ማኔጅመንት ሲስተም "Visitor Management System (VMS)" ምንድነው?** | **መ 2፡-** VMS የጎብኚዎችን የመንጃ ፈቃድ ወይም ከስቴት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ በስቴቱ የጾታዊ ጥቃት ወንጀለኝነት ተመዝግበው ከሆነ ለማጣራት ከመረጃ ቋት ላይ ይቃኛል። VMS በትምህርት ቤት ሕንፃ ውስጥ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ማንጠልጠል ያለባቸውን ስም የተጻፈበት መለያ ይሰጣል። |

## የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና አስፈላጊነት፡-

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ 3፡- በጎ ፈቃደኞች ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል? ለበጎ ፈቃደኞች እና ለኮንትራክተሮች የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን ስለማጤን እና ሪፖርት ማድረግ** | **መ 3፡-** አዎ። ትምህርት ቤቶችን እና ተማሪዎችን **በመደበኛነት** የሚደግፉ እና በመስክ ጉዞዎች የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች ሁሉም የበይነመረብ ሞጁል ማጠናቀቅ አለባቸው፣ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን ማጤን እና ሪፖርት ማድረግ ለበጎ ፈቃደኞች እና ለኮንትራክተሮች የሚሰጥ ሥልጠና ነው። የዚህ ስልጠና አስፈላጊነት በትምህርት ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎችን በመደበኛነት በበጎ ፈቃደኝነት በሚረዱ ሁሉ ላይ ይሠራል። |
| **ጥ 4፡- እኔ ይህንን ስልጠና እንዴት ማግኘት እችላለሁ?** | **መ 4፡-** ሥልጠናው በልጆች ላይ በደል እና ቸልተኝነት ድረ ገጽ ላይ እዚህ ይገኛል። |
| **ጥ 5፡- ማንኛውም ለትምህርት ቤት ድጋፍ የሚሰጥ/የምትሰጥ ሰው የስልጠና መስፈርቶቹን ማጠናቀቅ አለበ(ባ)ት?** | **መ 5፡-** ምንም እንኳን ሁሉንም የማህበረሰብ አባላት በዚህ ጠቃሚ እና መረጃ ሰጪ ስልጠና ላይ እንዲሳተፉ ብናበረታታም፣ በአሁኑ ወቅት **በቋሚነት** ትምህርት ቤቶችን የሚያገለግሉና የሚደግፉ **ግለሰቦች** ብቻ የህጻናት በደል እና ቸልተኝነትን በተመለከተ የሚሰጠውን ስልጠና እንዲወስዱ/እንዲያጠናቅቁ እንፈልጋለን። ነገር ግን፣ ይህ ግዴታ በት/ቤት ሰራተኞች ቁጥጥር በትላልቅ ዝግጅቶች ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ወይም ለአንድ ወቅት በዝግጅት የሚያግዙ ግለሰቦች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።የሚከተሉት የበጎ ፈቃደኛ ስልጠናን ማጠናቀቅ **የማይጠይቁ** የአገልግሎት አይነቶች ምሳሌዎች ናቸው (ይህ ዝርዝር ሁሉንም አያካትትም):-<br>• MCPS ሠራተኛ አብሯቸው እያለ(ች) በክፍል ውስጥ የሚሳተፉ እንግዳ አንባቢዎች እና ተናጋሪዎች።<br>• የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-የኮሌጅ መልማዮችና በጎፈቃደኞች በስራ እና በኮሌጅ አውደርዕዮች<br>• በዝግጅቱ ላይ የተገኙ ወይም በመርዳት ላይ የሚገኙ (ለምሳሌ:- የሠልፍ ትርኢት) ወይም ክፍል ውስጥ በተዘጋጀ ፓርቲ የሚረዱ ወላጅ/ሞግዚቶች ወይም ሌሎች ዘመዶች፣ እና<br>• በትልልቅ ሁነቶች-ዝግጅት የቲኬት መሸጫ ልዩ ዋጋ እና መደብሮች ላይ |

| | |
|---|---|
| | የሚሠሩ ወላጆች/ሞግዚቶች<br>MCPS [ስልጠና የሚያስፈልጋቸውን የተወሰኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አይነቶችን]() የሚገልፅ ሰነድ አዘጋጅቷል። |
| **ጥ 6፡- የበጎፈቃደኛ ስልጠና የሚገኘው መቼ ነው?** | **መ 6፡-** ሥልጠናው በልጆች ላይ በደል እና ቸልተኝነት [እዚህ]() ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። |
| **ጥ 7፡- MCPS የሚሰጠውን ስልጠና ቀደም ብዬ የጨረስኩ ቢሆንም፣ 2026-2027 የትምህርት ዘመን እንደገና መውሰድ ይኖርብኛል?** | **መ 7፡-** አንድ ግለሰብ ባለፈው ዓመት የተሰጠውን MCPS ስልጠና ማጠናቀቁ(ቋ)ን MCPS መዝግቦ ከሆነ፣ ያ ግለሰብ በዚህ የትምህርት ዘመን ተጨማሪ ስልጠና መውሰድ አያስፈልገውም/አያስፈልጋትም። **ስልጠናው መወሰድ ያለበት በየሦስት ዓመቱ ነው፡-**<br>● 2023-2024 ላይ ስልጠና የወሰዱ ከሆነ 2026-2027 ይወስዳሉ<br>● 2024-2025 ላይ ስልጠና የወሰዱ ከሆነ 2027-2028 ይወስዳሉ<br>● 2025-2026 ላይ ስልጠና የወሰዱ ከሆነ 2028-2029 ይወስዳሉ |
| **ጥ 8፡- በጎፈቃደኞች በሙሉ የስልጠና ሞጁሉን በድረ-ገጽ ማጠናቀቅ አለባቸው?** | **መ 8፡-** ሁሉም በጎ ፈቃደኞች የኤሌክትሮኒክስ ማረጋገጫ ለማግኘት ስለ ልጆች በደል እና ቸልተኝነት ድረ ገጽ ላይ ኦንላይን ሥልጠናውን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል [እዚህ]() ይህ መስፈርት መጠናቀቁን ለማረጋገጥ። አንድ በጎ ፈቃደኛ **'ስለ ህጻናት በደል እና ቸልተኝነት' (Child Abuse and Neglect) ስልጠናውን አስቀድሞ ያጠናቀቀ(ች) ከሆነ፣** ስሙ(ሟ) 'የበጎ ፈቃደኛ/ኮንትራክተር የስልጠና ማጠናቀቂያ ሪፖርት' (Volunteer/Contractor Completion Report) ላይ ይታያል። ሪፖርቱ የሚገኝበትን አገናኝ ሊንክ [MCPS Business Center]() (compliance) ስር ማግኘት ይችላሉ።<br><br><br>● **አንድ በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግል ሰው ስለ ህጻናት በደል እና ቸልተኝነትን የሚመለከተውን ስልጠና ካልወሰደ(ች)፣** ስልጠናውን ለመውሰድ መለያ አካውንት ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል። ወላጆች ወይም ሞግዚቶች የ MCPS Parent Portal አካውንት መጠቀም ወይም መክፈት ይችላሉ፣ ነገር ግን ወላጆች ያልሆኑት አካውንት ለመፍጠር ይችላሉ በዚህ [link]()። አንዴ አካውንታቸውን ካገኙ በኋላ፣ ስልጠናውን ለማጠናቀቅ እና ስለማጠናቀቃቸውም በኮርስ ስልጠና ላይ ሪኮርድ ሊኖራቸው ይችላል። በኮርስ ውጤት 100% ከተመዘገበ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ስልጠና መጠናቀቁን ማረጋገጫ ይሆናል። ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሰውን ሪፖርት ማግኘት ይችላሉ፤ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች የስልጠናውን ውጤትና ማጠናቀቃቸውን ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ ካስፈለጋቸው፣ ወደ ኮርስ ስልጠናው ውጤት ሪከርድ በመመለስ በማንኛውም ጊዜ መረጃውን ማግኘት ይችላሉ። በዚህ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅርጸት ምክንያት ትምህርት ቤቶች **ለበጎ ፈቃደኞች ወይም ለአነስተኛ ቡድን የሥልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ለመስጠት ኦንላይን ሞጁሉን እንደ መገልገያ የመጠቀም አማራጭ** አይኖራቸውም።<br>አኮሞዴሽን የሚያስፈልጋቸው ወላጆች/አሳዳጊዎች በትምህርት ቤቶች ከመሳተፍ አይታገዱም። ለአኮሞዴሽን ጥያቄዎች የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች (SLEA)፣በ 240-740-3977 ያነጋግሩ።<br>● MCPS [ስልጠና የሚያስፈልጋቸውን የተወሰኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አይነቶች የሚገልፅ ሰነድ]() አዘጋጅቷል። |
| **ጥ 9፡- የአካል ስንክልና ላለባቸው ስልጠና ለመሙላት "accommodations" የሚያስፈልገኝ ከሆነስ ምን ይደረጋል?** | **መ 9፡-** የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ እንደ አስፈላጊነቱ SLEA ጋር በመመካከር፣ በየራሳቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን ፍላጎት ተገቢ በሆነ መንገድ ማስተናገድ አለባቸው። [መ 8 ይመልከቱ] |
| **ጥ 10፡- የድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና በተለያዩ ቋንቋዎች ይሰጣል?** | **መ 10፡-** አዎ። በአሁኑ ጊዜ የኦንላይን ሥልጠና **እንግሊዝኛ፣ ስፓንሽኛ፣ ቻይንኛ፣** |

| | ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያንኛ፣ አማርኛ፣ ቬትናምኛ፣ እና ፖርቹጋልኛ ቋንቋዎች ይገኛል። |
|---|---|
| **ጥ 11፡- በጎፈቃደኞች ስልጠና ማሟላታቸውን እንዴት እናውቃለን?** | **መ 11፡-** በጎ ፈቃደኞች ሥልጠናውን ሲያጠናቅቁ በስልጠናው መሳተፋቸው ሪኮርድ ስለሚደረግ በ MCPS ይመዘገባል። አዲሱ አሠራር MCPS Parent Portal አካውንት ያስፈልገዋል፣ ስለማጠናቀቃቸው ማረጋገጫ 100% የኮርስ ውጤታቸው ላይ ይመዘገባል። ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሰውን ሪፖርት ማግኘት ይችላሉ፤ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች የኮርሱን ውጤትና ማጠናቀቃቸውን ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ ካስፈለጋቸው፣ ወደ ኮርስ ስልጠናው የውጤት ሪኮርድ በመመለስ በማንኛውም ጊዜ መረጃውን ማግኘት ይችላሉ። |
| **ጥ 12፡- በጎፈቃደኞች ስልጠናውን ከወሰዱ፣ ከተማሪዎች ጋር ይሠራሉ?** | **መ 12፡-** አዎ። ት/ቤት ባዘጋጀቸው የተለያዩ መንገዶች በጎፈቃደኞች ትምህርት ቤትን ለመርዳት ይችላሉ። |
| **ጥ 13፡- ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች የድረ-ገጽ ስልጠና መሙላት ይጠበቅባቸዋል?** | **መ 13፡-** አይደለም ካፍቴሪያ ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች እንደመደበኛ በጎፈቃደኛ አይቆጠሩም እና በዚህ ወቅት የ MCPS ሠራተኞች ይቆጣጠሯቸዋል። |
| **ጥ 14፡- ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪዎች በሚለቀቁበት ወቅት ወይም በእረፍት ሠዓት የሚረዱ ከሆነ ስልጠና መውሰድ አለባቸው?** | **መ 14፡-** አዎ፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ት/ቤት በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ከተማሪዎች ጋር የሚሠሩ ወላጆች/ሞግዚቶች በትምህርት ቤት ውስጥ በጎፈቃደኝነት ከመጀመራቸው በፊት በድረ-ገጽ ስልጠና ማሟላት አለባቸው። |
| **ጥ 15፡- ት/ቤትን የሚረዱ የ MCPS በጎ ፈቃደኛ - ተማሪዎች በድረ-ገጽ ላይ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | **መ 15፡-** አይደለም በትምህርት ቤት እየረዱ ያሉ የ MCPS በጎፈቃደኛ-ተማሪዎች ሁልጊዜም በ MCPS ሠራተኛ አማካይነት ቁጥጥር ይደረጋል። |
| **ጥ 16፡- ተማሪ መምህራን እና interns በድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | **መ 16፡-** አዎ። ተለማማጅ መምህራን እና ሰልጣኞች (interns)፣ [እዚህ] የሚገኘውን እና በመላው ዲስትሪክቱ የግዴታ የሆነውን የኦንላይን ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። |

## የጣት አሻራና የኃላ ታሪክ ማጣራት/ Background Check አስፈላጊነት/ግዴታዎች፡-

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ 17፡- ለበጎፈቃደኞች የበፊት ታሪካቸውን ማረጋገጫ መስፈርቶች/background check requirements ምንድናቸው?** | **መ 17፡-** በሚከተሉት ምድቦች ውስጥ ያሉት በጎ ፈቃደኞች የጣት አሻራ እና የበፊት ዳራ ማጣራት ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡-<br>● በጎ ፈቃደኛ አሰልጣኞች<br>● 6ኛ ክፍል በመስክ የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራሞች አጃቢዎች/ጠባቂዎች<br>● ከአካባቢው ውጭ (ከሮክቪል 50 ማይል ወይም ከዚያ በላይ ርቀት ላይ)) እና/ወይም ሌሊት የሚያሳልፉባቸው የመስክ ጉዞዎች ላይ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች<br>● ለረዥም ቀን ጉዞ የበጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ማጽደቅ የሚያስፈልገዉ። (ለምሳሌ፡- የጉዞ መነሻ ሠዓት MCPS ሥራ የሚጀመርበት ሠዓት እና/ወይም የመመለሻው ሠዓት 7:00 p.m በኋላ ከሆነ)<br><br>[ማሳሰቢያ -- በአንድ ቀን ጉዞ ከ 100 ማይል በታች የሚደረጉ የአትሌቲክስ ወይም የኪነ-ጥበብ ጉዞዎች፣ አጃቢዎች ወይም በፈቃደኝነት የሚሳተፉ ሰዎች የጣት አሻራ ወይም የዳራ ማጣራት (background check) እንዲያደርጉ አይጠየቁም።]<br>በስራ ላይ ያሉ የህግ አስከባሪ መኮንኖች (የአካባቢ፣ የስቴት፣ እና የፌዴራል) MCPS ከሚያደርገው የዳራ ማጣራት መስፈርቶች ነፃ ናቸው። ተጨማሪ መመሪያዎችን ለማግኘት Backroundscreening@mcpsmd.org ኢሜል መላክ አለብዎት። በደንቡ ልዩ ሁኔታ የተፈቀደላቸው ሠራተኞች (ለምሳሌ፡- የሕግ አስከባሪ አባላት፣ ወታደራዊ አባላት፣ የፌዴራል ሠራተኞች) ካልሆኑ በስተቀር MCPS ፈቃድ መስጫ ኮዶች (Agency Authorization #0000084571 እና ORI# MD920523Z) መሠረት የጣት አሻራቸውን መስጠት አለባቸው። BSO ጋር ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ፡- https://americanident.as.me/ ወይም በስቴት የተፈቀደለትን ቦታ |

| | |
|---|---|
| | ይጎብኙ፡- https://dpscs.maryland.gov/publicservs/fingerprint.shtml<br><br>MCPS ስልጠና የሚያስፈልጋቸውን የተወሰኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አይነቶችን የሚገልፅ ሰነድ አዘጋጅቷል። |
| **ጥ 18፡- በጎፈቃደኞች ስለበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ለማግኘት መሄድ ያለባቸው የት ነው እና ማጣሪያውን ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?** | **መ** 18፡- የጣት አሻራ እና የበፊት ታሪክ (ዳራ) ማጣራት መረጃ እዚህ ሊገኝ ይችላል። ቀጠሮ ያስፈልጋል፡-<br><br>850 Hungerford Drive, Room 137 Rockville, MD 20850<br>240-740-4670 ወይም Backgroundscreening@mcpsmd.org<br>የዳራ ማጣራት ሂደቱን ለማጠናቀቅ በግምት አራት ሳምንታት ይወስዳል። |
| **ጥ 19፡- የበጎ ፈቃደኞችን የበፊት ታሪክ ማጣራት ለማጠናቀቅ ማን ይከፍላል?** | **መ** 19: ለጣት አሻራ የሚደረገውን የዳራ ማጣራት ክፍያ $62.50 የመሸፈን ኃላፊነት የበጎ ፈቃደኛው(ዋ) ነው።<br>ለበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት የጣት አሻራ ማጣሪያ ወጪ እንዳይሳተፉ የሚያግድዎት ከሆነ፣ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይቻላል። ድጋፍ ለመጠየቅ፣ እባክዎ የክፍያ ድጋፍ መጠየቂያ ቅጽ ሞልተው ያቅርቡ። ከተፈቀደልዎት፣ ቀጠሮ ለማስያዝ BSO-CESC, 850 Hungerford Dr., Suite 137, Rockville, MD 20850 https://americanident.as.me/ ኢሜል ማድረግ አለብዎት።<br>• በመስክ የሚሰጥ ትምህርት (Outdoor Education) ላይ በአዳር ለሚሳተፉ አጃቢዎች (chaperones) የክፍያ መጠን $25.20 ዶላር ቅናሽ ይደረጋል።<br>• በአትሌቲክስ ዲፓርትመንት ድንጋጌ መሰረት፣ በበጎ ፈቃደኝነት የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች ለዳራ ማጣሪያ (background check) የሚወጣውን ወጪ መሸፈን አለባቸው። |
| **ጥ 20፡- ባለፈው ዓመት MCPS የዳራ ማጣራት (background check) አድርጌ ከነበረ፣ እንደገና ሌላ የዳራ ማጣራት ማድረግ ያስፈልገኛል?** | **መ** 20፡- በ 2019 ወይም ከዚያ በኋላ MCPS የዳራ ማጣራት ሂደት (የጣት አሻራ እና የህጻናት ጥበቃ አገልግሎት/CPS ቅጽ) ያጠናቀቁ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም የማህበረሰብ አባል ከሆኑ፣ ያኔ ያጠናቀቁት የዳራ ማጣራት (clearance) አሁንም ሊያገለግል ይችላል። MCPS የተማሪዎቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል፣ ቀጣይነት ያለው የዳራ ማጣራት ክትትል የሚያደርገውን የፌዴራል "Rap Back" (የእስር እና የክስ ታሪክ) የመረጃ ፕሮግራም ይጠቀማል።<br>ልጅዎ ከመጀመሪያው ማጣሪያ ጀምሮ MCPS ውስጥ ያለማቋረጥ ትምህርት እየተከታተለ(ች) ቆይቶ(ታ) ከሆነ፣ የእርስዎ ሁኔታ የሚያስፈልገው ማረጋገጥ ብቻ ነው። የማጣሪያ ሁኔታዎን ለማረጋገጥ እባክዎን የዳራ ማጣሪያ ቢሮ በሚከተለው ስልክ ቁጥር ወይም ኢሜል ይጠይቁ፡-<br>240-740-4670 ወይም ኢሜል/email: backgroundscreening@mcpsmd.org |
| **ጥ 21፡- የት/ቤት ወላጅ መምህር (ተማሪ) ህብረት (PTA/PTSA) ከትምህርት-በኋላ የሚከናወን እንቅስቃሴ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ፕሮግራም፣ ወይም ሌላ ፕሮግራም ስፖንሰር ቢያደርጉ፣ MCPS ኮንትራክተሮችን የሚመለከተው የበፊት-ዳራ ማጣራት እና የጣት አሻራ የማቅረብ መስፈርት እነዚህንም ይመለከታቸዋል?** | **መ** 21፡- በትምህርት ቤት ለሚካሄዱ ዝግጅቶች ብቻ የጣት አሻራ እና የዳራ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ።<br>• ከትምህርት ሰዓት ውጪ የሚከናወን ፕሮግራም MCPS የገንዘብ ድጋፍ የሚያደረግበት ወይም ስፖንሰር የሚደረግለት ከሆነ፣ ወይም MCPS የውሉ አካል ከሆነ (ማለትም፣ የርዕሰ መምህሩ ፊርማ በውሉ ላይ የሚገኝ ከሆነ)) እና ፕሮግራሙን የሚያቀርቡ አካላት MCPS ግቢ ውስጥ ከተማሪዎች ጋር ቀጥተኛ፣ ያለ ቁጥጥር እና ያለ ገደብ የመገናኘት እድል ያላቸው ከሆነ፣ የዳራ ማጣራት (background checks) እና ስልጠና መውሰድ የግድ አስፈላጊ ነው።<br>• ኮንትራቱ በት/ቤት ስፖንሰር ካልተደረገ እናብቸኛ ስፖንሰር አድራጊው PTA/PTSA ወይም ሌላ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም Interagency Coordinating Board/የወኪል ድርጅቶች አስተባባሪ ቦርድ (ICB) ሥር ከተደራጀ፣ MCPS የዳራ ማጣራት/background checks ወይም ስልጠና አይጠይቅም። ቢሆንም፣ PTA/PTSA ወይም ICB ለስራ ተቋራጮቻቸው ተጨማሪ ግዴታዎች ሊኖሯቸው ይችላል። |

| | |
|---|---|
| **ጥ 22፡- ለተጠባባቂ በጎ ፈቃደኞች ፍቃድ ማግኘታቸውን ወይም እንዳልተፈቀደላቸው የሚያሳውቀው ማነው?** | **መ 22፡-** በጎ ፈቃደኛ ለመሆን ያመለከቱ ሰዎች፣ ስለ ማመልከቻቸው ተቀባይነት ማግኘት/አለማግኘት ሁኔታ ከዳራ ማጣሪያ ቢሮ (Background Screening Office) በኢሜል ይገለጽላቸዋል። |
| **ጥ 23፡- ስለ በጎ ፈቃደኞች ሥልጠና እና የበፊት ታሪካቸውን ዳራ ማጣራት በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ማነጋገር አለብኝ?** | **መ 23፡-** ስለ በጎ ፈቃደኝነት መስፈርቶች ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት እባክዎን ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ።<br><br>በተጨማሪ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ ያልተነሱ ስጋቶችን በሚመለከት፡-<br>• **የበጎ ፈቃደኞች ስልጠና** ፡ የተማሪዎች አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጪ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ 240-740-3977<br>• **ዳራ ማጣራት** ፡ የጣት አሻራ መውሰጃ ቢሮ ለማግኘት 240-740-4670 Backgroundscreening@mcpsmd.org |
| **ጥ 24፡- በ MCPS ጣቢያዎች ላይ የሚሠሩ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞችን እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ይመለከታቸዋል?** | **መ 24፡-** ከጣምራ ምዝገባ (dual enrollment) ፕሮግራም/ACES ጋር የሚሰሩ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሰራተኞች፣ በሚቀጠሩበት ወቅት የጣት አሻራን ጨምሮ የወንጀል ታሪክ ዳራ የማጣራት ሂደት ይመለከታቸዋል። ትምህርት ቤት ባሉበት ወቅት ከሞንትጎመሪ ኮሌጅ የተሰጣቸውን የመታወቂያ ባጅ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ማድረግ አለባቸው። |
| **25- -የመንግስት ሠራተኞች (MCG) እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ሊተገበሩ ይችላሉ?** | **መ 25፡-** የጤና ክፍል ቴክኒሻኖች፣ ነርሶች፣ እና የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (DHHS) ሰራተኞች የሆኑት በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ የሚሰሩ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የመንግስት ሰራተኞች፣ በካውንቲው አስተዳደር (MCG) በኩል አጠቃላይ የወንጀል ታሪክ ዳራ ማጣራት ይደረግላቸዋል። እንደየሥራ ድርሻቸው፣ አንዳንድ ሠራተኞች MCPS ተጨማሪ የዳራ ማጣራት (background clearances) ማጠናቀቅ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አስፈላጊው ማጣራት ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ አኳኋን ወደ ትምህርት ቤት ህንጻዎች መግባትን በሚመለከት፣ ለተመደቡ MCG ሰራተኞች MCPS የደህንነት ጥበቃ ክፍል (MCPS Security) አማካኝነት የኮንትራክተር መግቢያ መታወቂያዎች ተዘጋጅተው ይሰጣሉ። |

**MCPS በጎ ፈቃደኞች**: https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership/volunteer.aspx

**MCPS የዳራ ማጣራት**: https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/security/fingerprint/

**የህጻናት በደል እና ቸልተኝነትን የተመለከተ ስልጠና:**
https://www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect/#Volunteer